የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.11
ADDIS ABABA, 4th January, 2017

**ማውጫ**

**አዋጅ** ቁጥር ፩ሺ፶፱/፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በጋና ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም ዘርፍ የትብብር ስምምነት ማፅደቂያ **አዋጅ**………….ገጽ ፱ሺ፱፻፸፯

CONTENT

Proclamation No. 1059/2017

Cooperation Agreement in the Field of Tourism between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Ghana Ratification Proclamation …………………...page 9977

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፱/፪ሺ፲

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጋና ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በቱሪዝም ዘርፍ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማጸደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጋና ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ ሰኔ ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION No. 1059/2017**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE COOPERATION AGREEMENT IN THE FIELD OF TOURISM BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF GHANA.**

**WHEREAS**, the Cooperation Agreement in the Field of Tourism between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Ghana was signed in Addis Ababa on the 23rd day of June, 2015

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified saidAgreement at its session held on the 2nd day of November, 2017;

**NOW,THEREFORE**, in accordance with article 55 sub articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በጋና ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም ዘርፍ የትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፱/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የ<u>ስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጋና ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም ዘርፍ ትብብር ለማድረግ ሰኔ ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>**

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣን ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ተሰጥቷል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Cooperation Agreement in the Field of Tourism between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Ghana Ratification Proclamation No…2017".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Cooperation Agreement in the Field of Tourism between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Ghana signed in Addis Ababa on the 23rd day of June, 2015 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Culture and Tourism is hereby empowered to implement this Agreement.

**4. <u>Effective Data</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 4th day of December, 2017**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRAT**
**REPUBLIC OF ETHIOPIA**